# <u>ኢትዮጵያን በጨረፍታ!</u>

ቁጥር-1

ከገረመው-በርሊን

ስለ አገራችን ጤናማ ወሬ መስማት በመጀመራችን እርስ በርሳችን የምስራች መባባል ይገባናል፡፡ የውጭ ሚዲያዎችም በውዴታ ነው ባይባልም ኢትዮጵያ እያደገች ነው የሚለውን ዜና አዘውትረው እየዘገቡ እንደሆነ እየተከታተልን ነው፡፡ በዓለማችን የኢኮኖሚ ዜናዎችን የሚያስነብበው ኢኮኖሚስት የተባለው ታዋቂ መፅሔት ሳይቀር ባለፉት 10 ዓመታት ኢትዮጵያ ባለ ሁለት አሃዝ እድገት ማስመዝገብዋን ዘግቧል፡፡ ስለ አገራችን ዕድገት ለመግለፅ የግድ የሌሎች ምስክርነት አስፈላጊ ነው ባይባልም ለአገራችን በጎ የማይመኙ ወገኖችም ሳይቀሩ እውነታውን ሊክዱት እንደማይችሉ ለማሳየት ብቻ ነው፡፡

ስለ አገራችን አዎንታዊና ገንቢ ዜናዎች ሲደመጡ እጢያቸው ዱብ የሚል ሌሎች ከአብራካችን የወጡ ወገኖች መኖራቸው ደግሞ አሳዛኝ ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ዋነኛ ጠላት ድህነት ነው፡ ድህነትን የመቀነስና የማጥፋት ጉዳይ የአገር አንድነት የመቀጠል እና ያለመቀጠል ጉዳይ ነው በማለት መንግስትና ህዝብ ወገብን የሚፈታተኑ የልማት ስራዎችን ለማስፈፀም ደፋ ቀና ሲሉ በተቃራኒው ቆመው ለገመድ ጉተታ ጨዋታ የተዘጋጁ እስኪመስል የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ጉዳይ አሳፋሪ ነው፡፡ በውጪም የሚኖሩ ወገኖቻችን ጋን በጠጠር ይደገፋል ብለው የአቅማቸውን ያህል ለማበርከት ጥረት ሲያደርጉ በጣም ጥቂት ጽንፈኞች ግን የአዳም ዘር እስኪገርመው ድረስ በተቃራኒው ቆመው የማደናቀፍ ፖለቲካ ሲያካሂዱ ይታያሉ፡፡

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውን በአገር ልማት ላይ የዓቅማቸውን ያህል አስተዋፅኦ እያደረጉ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ አንዳንዱቹ ወደ ሃገር ቤት ሄደው የመኖሪያ ጎጆ ቀልሰዋል፤ ሻል ያለ አቅም ያላቸው ደግሞ አነስተኛ የቢዝነስ/ ተቋም ከፍተዋል፤ በትምህርት የቀዩትም ሙያና ዕውቀታቸውን ይዘው በመሄድ ወገንና ህዝብን እያገለገሉ ይገኛል፤ ሌሎችም በሚኖሩብት ሀገር ሆነው በመንግስትና በህዝብ እየተሰሩ ያሉ የልማት ስራዎችን ይደግፋሉ፡፡ ይህም የሚመነጨው ድህነት የህዝብ ጠላት ነው የሚለውን አመለካከት ከወገናቸው ጋር እኩል በመጋራታቸው ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች የኢትዮጵያን ዲሞክራሲያዊ አንድነት ለማስቀጠል የሚቻለው የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ሲከበር እንደሆነ ጠንቅቀው ይረዳሉ፡፡ ድህነት በኢትዮጵ ገፅታ ላይ ጠባሳ ትቶ ማለፉን ከራሳቸው ተሞክሮ አይተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ስም ከድህነት እና ከርሃብ ጋር ብቻ አያይዘው የሚገልፁ የውጭ ዜጎች በስራና በትምህርት አለም አጋጥሟቸዋል፡፡ በመሆኑም ድህነት ከሀገራቸው እስኪወጣ የኢትዮጵያዊነት ወኔ እንደነሸጣቸው ይኖራል፡፡ ይሁንና ከዚህ ጎራ ወጣ በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ ግስጋሴ ለመግታት የቀቢፀ ተስፋ ፖለቲካ የሚያራምዱ እያየን መሆናችን ደግሞ “የእናት ሆድ--- “ የሚያስብል ነው፡፡

**ልዩነት እስከ የት?**

አሁን እየተናገርን ያለነው ስለ ፖለቲካ አመለካከት ልዩነት አይደለም፡፡ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት በተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች የመደራጀት ጉዳይ የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር አካል ከሆነ ሰንበትበት ብሏል፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአንድ ወገን የፖለቲካ አስተሳሰብ በሕዝብ ላይ ለመጫን የሚቻልባት አገር አይደለችም፡፡

የዚህ ምኞት አቀንቃኞች ህጋዊ አካሄድን ረግጠው በአውሮጳ ጎዳናዎች፣ መንግስታዊ ፅ/ቤቶች "ሰልፍ" እያሉ ሊኳትኑ ካልሆነ በስተቀር በአገራችን ዕድሉ ዝግ መሆኑን እነሱም ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ግን ደግሞ ማንነታቸውን ማወቁ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እነዚህ በበግ ለምድ የተጀቦኑ ተኩላዎች፣ የኢትዮጵያን ህዝብ የልማት ፍላጎት ረግጠው ለመቆም የከጀሉ፣ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ሸርከና ገጥመው ልማታችንን ወደ ኋላ ለመጎተት የሚተጉ ቡድኖችና ግለሰቦች ከወዴት የተገኙ ናቸው? ለምንስ ዓላማ? የኢትዮጵያ ብሄር ብሔረሰቦች እኩልነት ይከበር ሲባል አደባባይ ወጥተው የሚሞግቱት ለምን ይሆን? የኢትዮጵያ ህዝቦች በአባይ ወንዝ ያላቸውን ህጋዊና ታሪካዊ መብት ለማስከበር ደፋ ቀና ሲሉ ጋሬጣ ለመሆን የወሰኑት ለምን ዓላማ ይሆን? የሚሉ ጥቄዎች ሚዛናዊ ህሊና ካለው ወገን ሁሉ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ ከፖለቲካዊ ልዩነት ጋር ማያያዝ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በሀገር ክህደት ደረጃ የሚፈረጅ ክስተት ነው፡፡በመሰል ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቀው ከሚገኙ ወገኖች መካከል አሁንም ተጎትተው የገቡ የዋሆች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ነገር ግን ፅንፈኞችን አጅቦ መሄድ ራሱ በአገር ላይ የሚፈፀም በደል መሆኑን ከወዲሁ ቢያስተውሉ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያውያን መካከል የዝንተ አለም ክርክር፣ ውይይት እና የሃሳብ ፍጭት እንዲበለፅግ መስራትና ከፅንፈኛ ጋር ለአፍታም ቢሆን መቆም ለየቅል ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የዲያስፖራ አባላት ለታላቁ የህዳሴ ግድብ የሚሸጠውን ቦንድ ለማክሸፍ እየሞከሩ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለእነዚህ ወገኖች የኢትዮጵያ ህዝቦች የህዳሴውን ግድብ ግንባታ ሲጀምሩ "የነብር ጭራ አይዙትም፤ ከያዙትም አይለቁትም" በማለት ቆርጠው የተነሱ ስለሆኑ ማቆም፣ መግታት እንደማይቻል ማስታወስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህ ሃቅ እንዳለ ሆኖ ግን በህዳሴ ግድብ ላይ የሚደረገውን ህዝባዊ እንቅስቀሴ ለማደናቀፍ ጥረት ማድረግ በአገር ላይ የሚፈፀም በደል መሆኑ ልብ ያለው ልብ ይለዋል፡፡

**መልህቅ የሌላት መርከብ**

አሁን አሁን ደግሞ አሮጌ ፖለቲካ ለማደስ እተሞከረ ይገኛል፡፡ እነዚህ ወገኖች የፖለቲካ ሀሁ ስለጠፋባቸው በአገር ቤት የሚከሰቱ ለውጦችና ግድፈቶች ሳይለዩ ሲቃወሙ ይሰማል፡፡ አጀንዳ የለሽ ፖለቲከኞች ስለሆኑ መልህቅ እንደሌላት መርከብ በአገር ቤት በሚታየው የለውጥ ማዕበል ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ ሲላተሙ እያየን ነው፡፡ በአገር ቤት መንግስት የአገራችን የስኳር አቅርቦት ፍላጎትን ለሚሟላትና ብሎም ራስን ለመቻል ከተረፈም ወደ ውጭ ለመላክ እንዲቻል የስኳር ልማት ሲጀምር ሃይማትኖትን ሰበብ አድርገው ሲቃወሙ አድምጠናል፡፡ ቀጥለው በአዲስ አበባ እየተሰራ ካለው የቀላል ባቡር መንገድ የቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ ሐወልት ጉዳት እንዳይደርስበት ለጊዜው ተነስቶ ግንባታው ሲጠናቀቅ ወደ ቦታው ይመለሳል ሲባል የአምባጓሮ ያህል ሲጮሁ ተሰማ፡፡ በአገራችን የኤሌክትሪክ መቆራረጥ የመንግስት ድክመት ነው በማለት ሲያወግዙ የነበሩት ወገኖች ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሲጀመር "አባይን ለፖለቲካ ጥቅም ለማዋልና የዓረብ አብዮት ለማቆም" በማለት የተቃውሞ ድምፅ አሰሙ፡፡ የአገራችን ዕድገት በመደገፍ አንዳንድ ወዳጅ ሀገሮች የሚሰጡት ፋይናንስ እንዲያቆሙ ላንቃቸው እስኪነቃ ድረስ ዋይታቸውን አሰሙ፣ አሁን ደግሞ ተቆርቋሪ ነን ለማለት "ከቤኒሻንጉል ክልል አማራው እየተባረረ ነው" የሚል የአዞ እንባ እያስደመጡን ነው፡፡

የአገራችን ሕዝቦችና ብሔር ብሔረሰቦች በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በራሳቸው ፈቃደኝነት አዲስ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት እየገነቡ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የዜጎች ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር

መብት ያስከብራል፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት በአገር ደረጃ የነበሩ ቅራኔዎች በመፍታት በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ መንግስት እየገነባ ሲሆን በየጎጡና በየመንደሩ መለስተኛ የውሃ፣ የግጦሽ መነሻ ያደረጉ ችግሮች ሲከሰቱም ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ተቀምጦለት እየተፈታ ይገኛል፡፡ የፖለቲካ አክሮባት ለመስራት ብሎም ትርፍ ለማግኘት ካልተፈለገ በስተቀር በቤኒሻንጉል ተከሰተ የተባለው ችግርም መፍትሔ አግኝቷል፡፡ ይኸም ሆኖ ከዚህች ጉዳይ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መሞከር የአንድ ቁማርተኛ ግለሰብን ሁኔታ ያስታውሰናል፡፡ ቁማርተኛ ይዞት የነበረውን ገንዘብ እያጣ በሄደ ጊዜም አሁንስ በቃኝ ተሸንፌያለሁ አይልም ብቻ ሳይሆን አራጣ እየገባም ቢሆን ቁማር መጫወቱን ይቀጥላል፡፡

## ታዲያ ጩኸቱ ለምን?

ታዲያ እነዚህ ወገኖች ፍላጎታቸው ምንድነው ብላችሁ አስባችሁ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ እነዚህ ወገኖች ጥያቄያቸው አንድና ግልፅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተካሄደው የፖለቲካና ማህበራዊ ለውጥ ስራ አጥ ያደረጋቸው ወገኖች መኖራቸው መርሳት ተገቢ አይሆንም፡፡ ለአንድ ዘመን በስልጣን ላይ የቆዩ ሊሂቃንና የእነሱ ደቀመዛሙርት ከተቀመጡበት ዙፋን ዘጭ ብለው ስለተዘረገፉ በአሁኑ ወቅት ስራ ፈት ሆነዋል፡፡ እነሱ ደግሞ የተሞሉት “ሀገር ለማስተዳደር ተመርጠናል” በሚል የሞኝ ዘፈን ስለሆነ በሌላ ሙያ እምብዛም ናቸው፡፡ እነዚህ ወገኖች በፓርቲ ይደራጁ አይደራጁ አንድ የሚጋሩት አመለካከት ያላቸው መሆኑን የሚታወቅ ነው፡፡ ያጧትን ስልጣን መልሶ ማግኘት! ሆኖም ዴሞክራሲ ለእነዚህ ወገኖች ቦታ ነስቷቸዋል፡፡ የእነሱ አስተሳሰብም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ተቀባይነት የለውም፡፡ የነሱ የፖለቲካ አጀንዳ የተነጠቁትን ስልጣን መልሶ ማግኘት ሆኖ እያለ የሚንተራሱት ግን አንዴ ሃይማኖት ሌላ ጊዜ ብሔር ደግሞ ሌላ ጊዜ ሌላ እያሉ ዕድሜ ቀጥል ነገር መፈለጋቸው አይቀርም፡፡ የነሱ የፖለቲካ አቅማዳ ቀዳዳ ስለሆነ እስከ ነገ የሚዘልቅ ቋሚ አጀንዳ ከቶም ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም ወገን በያለበት አንድነት በብዙሐነት (Unity in diversity) በማለት ልዩነትን በሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር እያስታረቁ በመጓዝ ከፖለቲካ ልዩነት በላይ የሆኑትን አገራዊ ጉዳዮች በጋራ እንጠብቅ፡፡ ፅንፈኞች የተጎነጩትን የፖለቲካ ሃፍረትና መርዝ ወደ ሌላው ወገን እንዲረጩት መፍቀድ ግን በአንድነታችን ላይ የሚቃጣ አደጋ ስለአለው የእነዚህን ወገኖች አካሄድ አምረን ልንታገለው ይገባል፡፡

በቁጥር 2 ይጠብቁኝ

ጸሀፊውን በኢሜይል በ berlingeremew@gmail.com ያገኙታል።